በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-206828

ቀን፡-27/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ ወ/ሮ ሀለዊያ አብዱጀባር-ጠበቃ አቶ አውግቸው መኮንን ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡ 1. ሂላል አበዱጀባር
2. ካሊድ አበዱጀባር } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የአፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01-21392 ላይ ሚያዝያ 07/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀናበትን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአፈፃፀም አቤቱታ ቀደም ሲል ከአሁን ተጠሪዎች ጋር በዚያው ፍርድ ቤት በነበራቸው ክርክር ለክሱ ምክንያት ከሆነው ቤትና ይዞታ ላይ ለአሁን ተጠሪዎች እናት በፍርድ ቤቱ በፀደቀው ስምምነት ላይ ከተጠቀሰው ውጭ ባለው ቤት እና ይዞታ ላይ በስማቸው ካርታ እና ፕላን እንዲሰራላቸው ለክፍሉ ይዞታ አስተዳደር ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ይጠይቃሉ፡፡ ይህንኑ የአፈፃፀም አቤቱታ አስመልክቶ በአሁን ተጠሪዎች በኩል ምን መከራከሪያ እንደቀረበ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ በሌላ በኩል በዚህ የሰበር ሰሚ

ችሎት ክርክር ተካፋይ ያልሆኑት አቶ አህመድ መሃመድ የተባሉት ግለሰብ የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበት ቤት እና ይዞታ የአሁን ተጠሪዎች እና የራሳቸው አውራሽ የጋራ የውርስ ሀብት መሆኑን ጠቅሰው የአፈፃፀም አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 418 መሰረት አፈፃፀሙን በመቃወም ይቀርባሉ፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአፈፃፀም አቤቱታው የቀረበው ፍርድ ባረፈበት ንብረት ላይ ነው? ወይስ አይደለም?፣ የአፈፃፀም መቃወሚያውስ የቀረበው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች በመያዝ ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በውጤቱም በአሁን አመልካች እና ተጠሪዎች መካከል ቀደም ሲል የነበረው ክርክር በግራ ቀኙ ስምምነት ሲቋጭ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ በፀደቀው ስምምነት ላይ ክሰ ከቀረበበት ይዞታ ውስጥ ከይዞታው መግቢያ በር በስተቀኝ በኩል ካለው በምዕራብ ጌቱ ዮሐንስ፣ በሰሜን ዋና መንገድ፣ በደቡብ አፈወርቅ፣ በምስራቅ ሀወሊያ አብዱጀባር የሚዋሰነውን በአጠቃላይ በ689 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ የቤት ቁጥር 400.02፣ 4 ክፍል ሰርቪስ ቤት እና በፊት ለፊት ያለውን አንድ ትልቅ መጋዘን በውስጡ ስምንት ክፍል ያሉትን ጨምሮ የአሁን ተጠሪዎች እናት ለሆኑት ወ/ሮ ዘምዘም መሃመድ ለተባሉት ሰጥቻለሁ ከማለት ባለፈ የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበት ቤት እና ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ የእርቅ ስምምነቱም ሆነ ስምምነቱ የፀደቀበት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ አያሳይም፣ በእርቅ ስምምነቱ ወይም ስምምነቱ በፀደቀበት የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያልተመለከተ ንብረት ፍርድ ቤት በአፈፃፀም ሊያስገድድ የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ የአፈፃፀም አቤቱታው ውሳኔ ባላረፈበት ንብረት ላይ የቀረበ ነው፣ ለአፈፃፀም ተብሎ የታገደ/የተያዘ/ ንብረት በሌለበት የአፈፃፀም መቃወሚያ መቅረቡም አግባብ አይደለም በማለት የሁለቱንም አቤቱታዎች ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሚያዝያ 28/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/0121227 ላይ ህዳር 16/2009 ዓ.ም የመዘገበውን የግልግል ስምምነት ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪዎች የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ተጠሪዎች ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የተፃፈ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ቀደም ሲል ከአመልካች ጋር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/0121227 ላይ የነበራቸው ክርክር በግራ ቀኙ መካከል ህዳር 16/2009 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት መሰረት ስምምነቱ በፍርድ ቤቱ ፀድቆ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ የአሁን አመልካች አሁን የአፈፃፀም አቤቱታ ባቀረቡበት ንብረት ላይ የካቲት 05/2011 ዓ.ም ክስ አቅርበው ክሳቸው ውድቅ ተደርጎ እስከ ፌዴራል ጠቅላፍ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት በመ/ቁ/170628 ላይ መስከረም 28/2012 ዓ.ም የፀና በመሆኑ ክሱ ድጋሚ የቀረበ ነው፣ የአፈፃፀም አቤቱታውም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያጡትን መብት በእቅር ስምምነት ሽፋን በአቋራጭ ለመጎናፀፍ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ የአፈፃፀም አቤቱታ በቀረበበት ንብረት ላይም በፍርድ ቤት የተሰጠ ግልፅ ውሳኔ ባለመኖሩ አቤቱታቸው ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች በዚሁ ላይ የሚያቀርቡት የመልስ መልስ ካለ እንዲያቀርቡ እድል ቢሰጣቸውም በተያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ ያላቀረቡ በመሆኑ ይኸው መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመሰረቱ በፍርድ በተረጋገጠ መብት መሰረት የአፈፃፀም አቤቱታ የሚቀርበውም ሆነ በአቤቱታው መሰረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ የሚሰጠው ለአፈፃፀም አቤቱታው መሰረት በሆነው ፍርድ ላይ በግልፅ ፍርድ ባረፈበት ጉዳይ ላይ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 378 ይደነግጋል፡፡ አሁን በቀረበው ጉዳይ ለአመልካች የአፈፃፀም አቤቱታ መሰረት የሆነው በግራ ቀኙ መካል ህዳር 16/2009 ዓ.ም ተደርጎ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/121227 ላይ የፀደቀው የእቅር ስምምነት ነው፡፡ ለእርቅ ስምምነቱ ምክንያት በሆነው የፍርድ ቤት ክርክር ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እና የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ  የነበሩ መሆኑን፣ የእርቅ ስምምነቱም ክስ ቀረቦበት ከነበረው ይዞታ ላይ የአሁን አመልካች ከይዞታው መግቢያ በር ወደ ቀኝ ያለውን በአጠቃላይ 689 ካሬ ሜትር ይዞታ በላዩ ላይ ካለው ቤት ጋር ለአሁን ተጠሪዎች ወላጅ እናት ለሆኑት ወ/ሮ ዘምዘም መሃመድ የሰጧቸው መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት እና አጣሪ ችሎት አስቀርቦ ከመዝገብ ካያያዘው የእርቅ ስምምነት ሰነዱ ይዘት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስምምነቱ በዚህ መልኩ ለተጠሪዎች እናት የተሰጠውን ይዞታ እና ቤት ከመግለፅ ባለፈ ክስ ከቀረበበት ይዞታ ላይ በስምምነቱ ውስጥ ሳይጠቀስ ስለቀረው ይዞታ እና ቤት የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ በሌላ አገላለፅ ከስምምነቱ ውጭ ያለው ይዞታ እና ቤት የአሁን አመልካች ነው በሚል የተደረገ ስምምነትም ሆነ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡

በሌላ በኩል ይኸው ችሎት ተጠሪዎች በመልሳቸው ውስጥ የጠቀሱትንና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/170628 ላይ ተሰጥቷል የተባለውን መዝገብ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ በመዝገቡ ላይ አመልካች የነበሩት የአሁን አመልካች እራሳቸው ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የአሁን ሁለቱ ተጠሪዎች እና ሌላ አቶ አህመድ መሃመድ የተባሉ ግለሰብ ናቸው፡፡ በመዝገቡ ላይ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የነበረው ክርክር የተጀመረው የአሁን አመልካች በአሁን በተጠሪዎች ላይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከፀደቀው የእርቅ ስምምነት ውጭ ያለውን ይዞታ እና ቤት እንዲያስተዳድርላቸው ለአሁን 1ኛ ተጠሪ ውክልና ሰጥተው የውክልና ስልጣኑን ከሻሩት በኋላ ተጠሪው ይዞታ እና ቤቱን ሊያስረክባቸው ፈቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሶ በፍርድ ኃይል ተገዶ እንዲያስረክባቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በቀረበው ክስ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የአሁን አመልካች ክስ ካቀረቡበት ይዞታ እና ቤት ላይ መብት የላቸውም በሚል ክሱ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ይኸው ውሳኔ በየደረጃው ባሉት የበታች ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ በዚሁ ችሎት በመ/ቁ/170628 ላይ መስከረም 28/2012 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ፀድቋል፡፡

የአሁን አመልካች ለአሁኑ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው የአፈፃፀም አቤቱታ ያቀረቡት ከዚሁ በኋላ ነው፡፡ የአፈፃፀም አቤቱታው መነሻም ከእርቅ ስምምነቱ ውጭ ባለው ቤት እና ይዞታ ላይ በስማቸው ካርታ እና ፕላን እንዲሰራላቸው ለክፍሉ አስተዳደር ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡ ሆኖም የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበት ይዞታ እና ቤት የአመልካች ነው በሚል በእቅር ስምምነቱም ሆነ ስምምነቱ በፀደቀበት የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ እንዲያውም አመልካች የአፈፃፀም አቤቱታ ባቀረቡበት ንብረት ላይ የይገባኛል ክስ አቅርበው ከይዞታ እና ቤቱ ላይ መብት የላቸውም በሚል በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጭምር ተወስኗል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ አመልካች በግልፅ ፍርድ ያላረፈበትን ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤት ውሳኔ ጭምር አይገባቸውም ተብሎ ውሳኔ በተሰጠበት ንብረት ላይ የአፈፃፀም አቤቱታ ማቅረባቸው ከህግ አግባብ ውጭ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም የአፈፃፀም አቤቱታው የቀረበው ፍርድ ባላረፈበት ንብረት ላይ ነው በሚል ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/0121227 ላይ መጋቢት 10/2013 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ/01-21392 ላይ ሚያዝያ 07/2013 በተሰጠ ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም